# የኢትዮጵያን ወቅታዊና አሳሳቢ ችግሮች የመረመረ ሕዝባዊ ስብሰባ በለንደን ተካሄደ

ከንጉሤ ጋማ

**"በኢትዮጵያ ሁሉም ነገር ይሸጣል፣ ልጆቻችንና እህቶቻችን ጭምር" አባንግ ሜቶ**



በወቅቱ የኢትዮጵያ አሣሣቢ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የተወያየ ሕዝባዊ ስብሰባ እሁድ ጥር 23 ቀን 2002 ዓ ም በለንደን ከተማ ተካሄደ። በዚሁ ስብሰባ ላይ በተጋባዥነት ተገኝተዉ ንግግር ያደረጉት ዕዉቁ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አባንግ ሜቶ ባደረጉት ሰፊ ገለፃ በኢትዮጵያ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በረሃብና በምግብ ዕጥረት በመሰቃየት ላይ እንደሚገኝና ረሀብ የምንታወቅበት ዓለም አቀፍ መገለጫችን እንደሆነ አብራርተዋል። በ1984 ዓ ም ተከስቶ በነበረዉ የረሃብ አደጋ በወቅቱ የነበረዉን የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለ ማርያም አገዛዝ ሲኮንኑ የነበሩት የዛሬዎቹ ባለስልጣናት አገሪቱን ለከፋ ረሃብ እንዳጋለጧት በማስረጃ አስደግፈዉ አሳይተዋል። አቶ አባንግ የትዉልድ ስፍራቸዉ በሆነዉ የጋምቤላ ክልል ያለዉን የምግብና የመሠረተ ልማት ችግር ከካናዳ መንግስት አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ለመርዳት ጥረት ቢያደርጉም የወያኔ መንግስት ትግራይ ዉስጥ እስካልተንቀሳቀስህ በሚል ምክንያት ፈቃድ እንደከለከላቸዉ አብራርተዉ፣ ያ የተወለዱበትና ያደጉበት አካባቢ ሕዝብ የልማት ተጠቃሚ እንዳይሆን ከመደረጉም በላይ በአሁኑ ወቅት አልፎ ተርፎ እትብቱ ከተቀበረበት መሬት ያለፍላጎቱ በኃይል እየተፈናቀለ መሬቱ ለሳዑድ አረቢያ፣ ለሕንድ፣ ለማሌዥያ፣ ለሼህ አላሙዲን እና ለሌሎች ኩባንያዎች በሄክታር በርካሽ ዋጋ በመቸብቸብ ላይ መሆኑን በምሬት ገልፀዋል።

በሕዝቧ ላይ የረሃብና የምግብ እጥረት አደጋ እያንዣበበ ባለበት ወቅት ገበሬዉን ከመሬቱ በማፈናቀል በኢንቬስትሜንት ስም ለባዕዳን ከበርቴዎች መሬቷ በመሸጥ ላይ ያለች ብቸኛ አገር ኢትዮጵያ መሆኗን በአፅንዖት አስገንዝበዋል። ለወያኔ ጥቅም የተገዛዉ የክልሉ ፕሬዝዳንት ተብዬ ካድሬ ከፌዴራሉ መንግስት የግብርና ሚኒስቴር ጋር በመመሳጠር ገበሬዉን እያፈናቀለ ሸያጩን በማጧጧፍ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዉ፣ለዘመናት የአካባቢዉን ልምላሜና የአየር ንብረት ሲጠብቁ የነበሩ የክልሉ ደንና ትላልቅ ዛፎች በሚያሳዝን ሁኔታ በመመንጠር ላይ እንዳሉ ተናግረዋል። አቶ አባንግ ከዚሁ ጋር በማያያዝ በነፃነት ትግሏ በመላዉ የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ዉስጥ አኩሪ ስፍራ ያላት፣ በጥንታዊነቷና በታላቅነቷ የምትታወቀዉ አገራችን ሕዝቦቿ ሰብዓዊ መብታቸዉ ተረግጦ፣ ፍትህ አጥተዉ ሲገደሉና በየእስር ቤቱ ሲሰቃዩ፣ ረሃብ እያንዣበበ ባለበት ወቅት ለም መሬቶቿ ለባዕዳን ሲቸበቸብ፣ በሌላም በኩል የግዛት አንድነቷ ያለህጋዊ

ዕዉቅና ሲሸረሸር፣ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ በዝምታ ከማየት በስተቀር የሚያደርገዉ ነገር እንደሌለ አስረድተዋል።
የወያኔ ቡድን የኢትዮጵያዊነት ስሜት የሌለዉ፣ አንድነቷን እንዲያፈርስ በረቀቀ ዘዴ በኢትዮጵያ መሰረታዊ ጠላቶች የተቋቋመና በነሱም እየተረዳ ወደ ሥልጣን የመጣ በመሆኑ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ይታደገናል፣ ከዚህ አደጋ ያወጣናል ብለን መጠበቅ የዋህነት እንደሆነ አቶ ኦባንግ በሠፊዉ ተንትነዋል።

መለስ ዜናዊና ጥቂት ከሃዲ ግብረ አበሮቹ በዚህ ዓይነት ከቀጠሉ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊያን የሚባሉ ሕዝቦች በቀጣይነት መኖራቸዉ አጠያያቂ እንደሆነ ገልፀዉ፣ ኢትዮጵያን ማዳን የኢትዮጵያዊያን ብቸኛ ቀዳሚ ተግባር መሆን እንዳለበት አበክረዉ አስገንዝበዋል። ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን በየመን፣ በሳዑዲ፣ በሊቢያ፣ በቤይሩትና በሌሎችም አገሮች በመሰደድ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደሰዉ በማይቆጠሩበት ደረጃ ላይ መድረሳቸዉንም አቶ ኦባንግ አልሸሸጉም። ከዚህና ከሌሎችም እዉነታዎች በመነሳት ይህ ግፍና በደል ሲፈፀም፣ አቅም በፈቀደ በጋራ በመነሳት ለችግራችን እልባት ለመስጠት ሞራል ያጣንበት ምክንያት ምንድነዉ? በማለት ተሰብሳቢዉን ጠይቀዋል። ነፃነታችንን ለማስከበር አሻፈረን ብለን እንዳንነሳ የሚያደርገንን፣ በአገራችንና በወገናችን  ላይ ዘግናኝ ስቃይ ሲደርስ ዓይናችን እያየ ባይተዋር የሆንበትን ሚስጥር ማወቅ ይኖርብናል፣ በአገርና በወገን ጉዳይ ተቆርቋሪ ሆነን እንደሕዝብ በአንድ እስካልቆምን ድረስ፣ እንደሕዝብ ልንኖር እንደማንችል ጠንቅቀን ልንረዳዉ ይገባል ብለዋል።
አገር ከሌለ ሕዝብ የለም፣ ስንወለድ ጎሣና ቋንቋ ብሎ ነገር አልነበረም እናም ኢትዮጵያዊነት ግንዳችን መሆኑን በእርግጠኝነት ልንቀበለዉ፣ ዘርና ጎሳ ከኋላ የመጡ ተቀጥላ ቅርንጫፍ እንደሆኑ ማመን ይኖርብናል ካሉ በኋላ ከ80 በላይ የሆነዉ የብሔረሰብ ቀለማችን፣ አገራችንን የተለያዩ ህብረ ቀለማት ባሏቸዉ አበቦች የደመቀች የመናፈሻ ስፍራ አድርገን እንድንመለከታት እግዚአብሔር የመረጠን ሕዝቦች ነን በማለት በማንነታቸዉ የሚሰማቸዉን ክብር ተናግረዋል።  የኦሮሞዉ፣ የአማራዉ፣ የከምባታዉ፣ የአኝዋኩ፣ የከምባታዉ፣ የሌላዉም ነፃነት በእኩልነት እስካልተከበረ ድረስ ሁላችንም ነፃነት እንደሌለን መገንዘብ ይኖርብናል ብለዋል።
በንግግራቸዉ ማጠቃለያ ላይ የቡና ጀበና በመያዝ ከቅርፅዋ አንስቶ ከኢትዮጵያ የቀድሞ ካርታ ጋር ያላትን መመሳሰል ከፍ አድርገዉ በማሳየት በወያኔ አምባገነን መሪዎች አፍራሽ ተግባር ከጊዜ ወደጊዜ ስር  እየሰደደ በመሄድ ላይ ላለዉ አሳሳቢ ችግር ኢትዮጵያዊያን እጅ ለእጅ ተያይዘን በጋራ መፍትሔ ለመሻት እስካልቆምንና እስካልጠበቅናት ድረስ የወደፊቱ የአገራችን ዕጣ ፈንታ እንደዚህ ሊበታተን ይችላል በማለት እንባ እየተናነቃቸዉ የያዙትን ጀበና ለቀዉታል። በጀበናዉ በያቅጣጫዉ መበታተን የቀረበዉ ተምሳሌት በአዳራሹ በነበረዉ ተሰብሳቢ ላይ በቃላት ለመግለፅ የማይቻል የሀዘን ስሜት ፈጥሯል።

ከአቶ ኦባንግ ገለፃ በኋላ ከተሰብሳቢዎች የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። ከነዚህም መካከል አንደኛዉ ተሰብሳቢ ወያኔ ወደስልጣን ከመጣበት ወቅት አንስቶ ብሄራዊ ዉርደት እየደረሰብን እንደሆነ፣ የሰለጠነ ፖለቲካ በሚካሄድበት አዉሮፓ ዉስጥ እያለን ልንማር አለመቻላችን እንደሚያሳዝናቸዉ ገልፀዋል። ሁልጊዜ እናወራለን፣ ከምርጫ 97 በኋላ በርግጥ እንዳለቀለት የተረዳነዉ የወያኔ ከሃዲዎች ለዛሬ ሳይሆን በቀጣይነት የወደፊት መጥፊያችንን ሲደግሱልን እኛ በአንድነት በመቆም ግባችንን ማስቀመጥ አለመቻላችን እጅግ ያሳዝናል በማለት እንባ እየተናነቃቸዉ ገልፀዋል።  ሌላዉ ተሰብሳቢ በበኩላቸዉ ወያኔ ከመጀመሪያዉ አንስቶ ኢትዮጵያዊ መንግስት እንዳልሆነ የገለፁ ሲሆን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ ኃላፊ ሆነዉ በሚሰሩበት ወቅት በ1986 ዓ ም የረሀብ አደጋ ባንዣበበት የወላይታ አካባቢ ሕዝብ ከፍተኛ ተጠቂ ሆኖ ለከፍተኛ

ዕልቂት በተጋለጠበት ወቅት ለደቡብ ክልል 22 ሺህ ኩንታል የሚሆን የርዳታ እህል በፌዴራል ደረጃ ሲመደብ ለትግራይ ክልል ግን 1.3 ሚሊዮን ኩንታል እንደተሰጠ የሚያዉቁ መሆናቸዉን ለምሳሌ ያህል ጠቅሰዉ ወያኔ አነሳሱም ሆነ አደረጃጀቱ ትግራይን ነፃ ለማዉጣት እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል ብለዋል፡፡
መንገድ ከፍተን መሸጋገሪያ ሆነን ያመጣነዉ እኛ ነን፣ ዛሬም አንድ ሆነን መቆም ባለመቻላችን በመለስ ፈቃድና ሙሉ ቁጥጥር ስር ወድቀናል፣ የአገራችንም አንድነት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፣ ነገ ኦጋዴንንም አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህን አፍራሽ ተግባር በጋራ መታገል ሲገባን እኛ እዚህ የእግዚአብሔር ሠላምታ ለመለዋወጥ እንኳ አንደፍርም፡፡ እጅግ የሚያሳዝነዉ አገር ቤት ዉስጥ ላለዉ ወጣት ሞዴል ሆነን መታየት ያለመቻላችን ነዉ ብለዋል፡፡
ሌላይኛዋ ተሰብሳቢ በበኩላቸዉ ሠላይና ተሠላይ፣ ልጅና የእንጀራ ልጅ በሆንበት፣ አመለካከታችን እጅግ በተለያየበትና እርስ በርሳችን በየጥቃቅኑ ምክንያት ጣት እየተጠ ነቋቆልን ባለንበት ሁኔታ ስለአገር ነፃነት እንዴት መነጋገር ይቻላል? አገር ቤት እየተሰቃዩና እየተሸሎኮለኩ በሚኖሩ ዘመዶቻችን ጫማ ዉስጥ እራሳችንን አድርገን እስካላየን ድረስ ተሰብስበን ፋይዳ ያለዉ ስራ ለመስራት አንችልም፡፡ በአንድነት መቆምና መነሳት ከቻልን ግን ወያኔ ከህግ ዉጭ በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የሚፈፅመዉን ወንጀል በተባበሩት መንግስታትና በሌሎችም አካላት አማካይነት አጋልጠን ዓለም አቀፍ ህግ በሚፈቅደዉ መሰረት ፍትህ ልናገኝ እንደምንችል በማጣቀስ አስረድተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕዉቅናና ይሁንታ በሌለበት መልኩ የወያኔ አምባገነን መሪዎች ዛሬ በየደረጃዉ የአገራችንን የግዛት አንድነት በመሸርሸርና ዜጋዉን እትብቱ ከተቀበረበት በኃይል በማፈናቀል፣ በኢንቬስትሜንት ስም ለባዕዳን ከበርቴዎች የሚቸበችበዉ የመሬት ሽያጭ በቀላሉ መታየት እንደሌለበት አንድ ተሰብሳቢ የዛሬዋ ጅቡቲ በኮንትራት ፣ እንዲሁም ሡልጣን ኢብራሂም ለተባለ ግለሰብ የአሰብ ቁራጭ መሬት በሽያጭ የተሰጠበትን ሁኔታና እነዚህ ያስከተሏቸዉን ዉጤቶች ታሪክ በማጣቀስ አስገንዝበዋል፡፡ ድርጊቱ በዝምታ ከታለፈ በሂደት ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳትኖር የሚያደርግ መሆኑ አያጠራጥርም ብለዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለዉጥና መሻሻል አለ፣ ኢንቬስትሜንት አለ፣ ሠላማዊ ትግል ማካሄድ ይቻላል፣ በምርጫ መሳተፍ እንችላለን ብለዉ የሚገምቱ ሁሉ በስልጣን ላይ ላለዉ መንግስት ተጨማሪ ጊዜ ከመስጠት ባሻገር ምንም እንደማይፈይዱ መልዕክቱ ሊደርሳቸዉ ይገባል፣ መለስ ብቻ ሳይሆን እነሱም አገር በማፍረስ ወንጀል ከተጠያቂነት እንደማይድኑ ሊረዱት ይገባል በማለት አስጠንቅቀዋል፡፡

ከራሳቸዉ አልፎ ለሌሎች የአፍሪቃ ጥቁር ሕዝቦች መብትና ነፃነት ይታገሉ የነበሩ አባቶቻችንን ሆነን መገኘት ከተሳነን እኛ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዜጎች በፈቃዳችን መዋረድ መብታችን ነዉ በማለት አስተያየት የሰጡት ተሰብሳቢ፣ ወያኔም ሆነ ሌሎች ቡድኖች ሕዝብን ነፃ ለማዉጣት የተደራጁ ሳይሆን አገራችን በቅኝ ግዛት ተይዘዉ ለነበሩ በርካታ የአፍሪቃ አገራት ነፃ መዉጣት ስትታገል የነበረች በመሆኗ ፀረ አፍሪቃ የሆኑ ኃይሎች በባንዳነት እንዲያገለግሏቸዉ ለስዉር ዓላማ ያቋቋሚቸዉ ጠላቶቻችን ናቸዉ ብለዋል፡፡ ወያኔ ሶማሊያን የወረረበትን ሁኔታ በጥንቃቄ ልናጤነዉ ይገባል፡፡ አንድ ሆነን በጋራ ከመቆም ይልቅ ወያኔን ለመዋጋት የተነሱ ኃይሎችን አዳክመናል፣ አሳልፈንም ሰጥተናል ካሉ በኋላ ለመብቱ፣ ለነፃነቱና ለአገሩ ለመሞት የቆረጠ ጀግና ሕዝብ ስላለን፣ ባለፈዉ ሳንቆጭ፣ ጊዜ ሳናጠፋ ደካማ ጎናችንን በማስወገድ እራሳችንን በአዲስ መልክ አደራጅተን አገርና ወገንን ለመታደግ መነሳት አለብን በማለት አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ኦባንግ ሜቶ የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የወዳጅነት ንቅናቄ /Solidarity Movement of New Ethiopia/ SMNE/ በሚል ስያሜ ባቋቋሙት ድርጅታቸዉ አማካይነት ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ ዲሞክራሲያዊ ዕድገት የሚጠየቁትን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸዉን በመግለፅ አጋጣሚዉ የፈቀደልን በያለንበት ተቀራርበን ለመስራት የተጠናከረ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል፣ ይህንን ካደረግንም እግዚአብሔር ይረዳናል ብለዋል።